# በኢ.ኦ.ተ.ቤ ሥር ያሉ ገዳማትንና ቅዱሳት ሥፍራዎችን በማስተዋወቅ ረገድ የፎክሎር ጥናቶች ሚና

የኔዓለም አረዶ[1] እና ዕሤተ ታደለ[2]


Abstract

The main purpose of this study is to find out the contribution of research works focusing on religious issues in promoting Ethiopian Orthodox Tewahido religious institution. The research works which were selected for this study were conducted for the partial fulfillment of Bachlor and Masters degrees in the department of Amharic Language, Literature and Folklore, Addis Ababa University. Amongst the research works focusing on religious issues specifically those on oral literature and material culture were selected purposefully. The research sites were selected using convinient sampling technique. A total of 29 research works were found. From these 12 research works were identified by using document analysis. Six are on oral literature, three are on material culture; and the rest three are focused on both material culture and oral literature. Data were organized thematically and analyzed using descriptive analysis method. The analysis showes that, the research works especially those on oral literature (narratives), mention the name of monastery being studied in the research title; this is where the contribution begins. Narratives in the oral literature researches presented ancientness or history, holiness, entirety, the miracles of the church and monasteries under study. Material culture researches focused on holy/ sacred/ objects. Mentioning the names and interpreting the symbolic significance of those objects was the focus of those researches. The analysis reveales that those research works played great role in promoting different churches and monasteries located in different areas. Therefore, the researchers of this study recommend that it is better if such trend of research will continue in the future.


Key Terms: Religion, EOTC, research works, roles, promotion.


[1] በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህርት፣ በቁሳዊ ባህል ረዳት ፕሮፌሰር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ Email: yenealem.aredo@aau.edu.et

[2] በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህርት፣ በሥነ ቃል ኤም.ኤ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ Email: Email:essietetadele@gmail.com

## ፩. መግቢያ

ይህ ጥናት ከፎክሎር ጥናት ዘርፎች መካከል መሠረታቸውን ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ያደረጉ በተለይም ሥነ ቃል እና ቁሳዊ ባህል ላይ ያተኮሩትን ጥናቶች በመለየት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር ያሉ የተቀደሱ ሃይማኖታዊ ሥፍራዎችን በማስተዋወቅ ረገድ የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ የሚቀኝ ነው (ፈቃደ፣ ፲፱፻፺፩)። ሥነ ቃልና ቁሳዊ ባህል የተመረጡበት ምክንያት በጥናቶቹ ቅዱሳት መካናቱን የተመለከቱ ቃል ተረኮች እና ቃል ግጥሞች ይዘቶች ተተንትነው የቀረቡ በመሆኑ በቁሳዊ ባህል ረገድም የንዋየ ቅድሳቱ ተምሳሌታዊ ትርጓሜ የተገለጸ በመሆኑ ቅዱሳት መካናቱን የተመለከቱ መረጃዎችን በመውሰድና ማሳያዎችንም ለአንባቢ በማቅረብ የጥናቶቹን አበርክቶ ለማሳየት ስለሚያስችሉን ነው።

የሃይማኖት ፎክሎር ጥናት በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል (ትምህርት ክፍሉ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ በመባል ይታወቅ እንደ ነበር ልብ ይሏል) በርካታ አሥርት ዓመታትን ያስቆጠረ የጥናት አቅጣጫ ነው። ዐብይ (፲፱፻፷፫) እንዳስቀመጡት፣ ከቤተ መጻሕፍት ድርሳናት ፍተሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በ(፲፱፻፷፫) ዓ.ም. የሃይማኖታዊ ፎክሎር ጥናት በዚሁ ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ነው። በዚሁ ትምህርት ክፍል በየጊዜውም በተለይ “የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር” በሚል ስያሜ በሚታወቀው የሁለተኛ ዲግሪ[3] መርሐ ግብር የተመራቂ ተማሪዎች የጥናት ትኩረት በመሆን አሁን ድረስ ልዩ ልዩ ጥናቶች እየተካሄዱ ይገኛሉ። በእነዚህ ጊዜያት የተካሄዱት ሃይማኖት ተኮር የፎክሎር ጥናቶች ግባቸው በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የሚስተዋሉ ፎክሎራዊ (ባህላዊ) ጉዳዮችን ነጥሎ ማሳየት[4] ነበር፤ ነውም። በሌላ በኩል እኒሁ ጥናቶች የሃይማኖት ስፍራዎችን፣ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማትን በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ ሚና አላቸው።

በቤተመጻሕፍት በተደረገ ፍተሻ የሃይማኖት ስፍራዎችን በተናጠል ያጠኑ እንጂ ሃይማኖቱ እና የፎክሎር መስክን ተዛምዶ ወይም ጥናቶቹ ለሃይማኖት ተቋሙ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ የተመለከተ ጥናት አልተገኘም። ይህ ጥናት የተመሠረተበት ዋና

[3] ለዚህ ጥናት ዓላማ በተደረገ ፍተሻ በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ የተሠሩ ጥናቶች የተገኙት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከቀረቡት ይሁን እንጂ በትምህርት ክፍሉ የፎክሎር ትምህርት በሦስተኛ ዲግሪም እየተሰጠ ይገኛል።

[4] በዚህ ጥናት “ሃይማኖታዊ ፎክሎር” የሚለው እሳቤ የጥናት ሥራዎቹ ምንጭ(መገኛ) ከፎክሎር የጥናት አቅጣጫዎች የትኛው ነው? የሚለውን ለማሳየት የዋለ እንጂ ሃይማኖት የፎክሎር አካል ነው ወደሚል አዝማሚያ የሚያመራ አይደለም። ጥናቱ ይህን የአጠና መንገድ ጉዳዩ አድርጎ የተካሄደ እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

ምክንያትም እነዚህ ጥናቶች ለተመረጠው የሃይማኖት ተቋም ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እንዲሁም የፎክሎር መስክ እና የሃይማኖት ተቋሙን የእርስ በርስ ተዛምዶና ትስስር ማሳየት መፈለጉ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ጥናቶችን ለአንድ የጋራ ጉዳይ በመረጃ ምንጭነት መጠቀም የበርካታ ጥናቶችን መረጃ በአንድ ድርሳን ለማግኘት ያስችላል፡፡ በዚህ ሐሳብ መነሻነት በተመሳሳይ መንገድ ለሚካሄዱ ሌሎች ጥናቶች መነሻ ይሆናል ተብሎ መታሰቡ ለዚህ ጥናት መካሄድ ሌላው ምክንያት ሆኗል፡፡

ከላይ በቀረበው ሐሳብ መሠረት ይህ ጥናት የሚከተሉት የምርምር ጥያቄዎች ላይ ተመሥርቷል፡፡ በሃይማኖት ፎክሎር ሥነ ቃልና ቁሳዊ ባህል ላይ የተጠኑ ጥናቶች የትኞቹ ናቸው? በቁሳዊ በሥነ ቃል እና ባህል ላይ የተጠኑት ጥናቶች ለሃይማኖት ተቋሙ ምን አስተዋጽኦ አበረከቱ? አበርክቶአቸውስ በምን በምን መንገድ ተገለጸ? የሚሉት ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሥር የሚገኙ ሃይማኖታዊ ስፍራዎች ቃላዊና ቁሳዊ ቃላዊ ሀብቶችን በማስተዋወቅ ረገድ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተካሄዱ የሃይማኖታዊ ፎክሎር ጥናቶችን ሚና ማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ንኡሳን ዓላማዎቹም፡-

- ሃይማኖታዊ ስፍራዎችን በማስተዋወቅ ረገድ የተሠሩ ጥናቶችን መለየት፤
- የጥናት ሥራዎቹን የትኩረት አቅጣጫ ማሳየት፤
- የጥናት ሥራዎቹ ለሃይማኖት ተቋሙ ያላቸውን አበርክቶ መግለጽ፤

በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በሃይማኖታዊ ፎክሎር ዘርፍ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት፣ አብነት ትምህርት ቤቶች፣ የቤተ ክርስቲያናትና ቅዱሳን ስፍራዎችን አመሠራረት የተመለከቱ ተረኮች፣ በክህነት ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓት ላይ እና በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የቀረቡ ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ ይህ ጥናት ከነዚህ ጥናቶች ውስጥ በተረኮች[5]፣ በቃል ግጥም[6] እና በንዋየ ቅድሳት ላይ የቀረቡ ጥናቶች ላይ ተወስኗል[7]፡፡

[5] በሥነ ቃል ዘርፍ አከፋፈል ከአፍአዊ ዝርው ትረካ ሥር ይመደባል፡፡

[6] በሥነ ቃል ዘርፍ አከፋፈል ከሚዜሙ ወይም የሚገጠሙ ውስጥ የምስጋና እና የተማጽኖ ቃላዊ ግጥሞችን ይመለከታል፡፡

[7] በሃይማኖታዊ ፎክሎር አራቱ የፎክሎር ዋና ዋና ዘርፎች የጥናት ትኩረት ተደርገው ይጠናሉ፤ በዚህ ጥናት ሁሉም ጥናቶች ቢካተቱ ጉዳዩ ሰፍቶ ከሚፈለገው የገጽ ብዛት እንዳያልፍ በመስጋት፣ ጥልቀት ያለው ጥናትም ለማካሄድ በመፈለግ በዋናነት ሥነ ቃልና ቁሳዊ ባህል ላይ የቀረቡ ጥናቶች ላይ ለመወሰን ፈቅደናል፡፡

ይህ ጥናት መካሄዱ በዋናነት ተተኳሪ የሆኑት ሁለቱ ተቋማትን ይጠቅማል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በርእሱ እንደተገለጸው ለዚህ ጥናት የተመረጡትና የባህል ጥናት በሆነው ፎክሎር ዘርፍ የተጠኑ ጥናቶች ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው በመሆናቸው የሃይማኖት ተቋሙን ለአማኙም ሆነ ከሃይማኖቱ ውጪ ላለው ማኅበረሰብ በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ እንዲሁም በፎክሎር የጥናት መስክ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች የሚጠኑ መሆናቸውን በማሳየት ረገድም በሃይማኖታዊ ፎክሎር ዘርፍ በሌሎች ሃይማኖቶች ላይ የተጠኑ ጥናቶች አበርክቶዎች እንዲጠኑ መነሻ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በመስክ ጥናት የተካሄዱ ጥናቶች በሰነድ ፍተሻ በመጠቀም የቀጣይ ጥናት ጥሬ መረጃ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለሌሎች አጥኚዎች በማሳየት ረገድ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱን አግኝተው ማንበብ ለሚችሉ ልዩ ልዩ አካላት ማለትም በዘርፉ ላይ ምርምር የሚያደርጉ አጥኚዎች፣ በቤተ ክርስቲያኗ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ባለሙያዎች፣ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባለሙያዎች በልዩ ልዩ ገዳማት እና አድባራት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች በአንድ ሰነድ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡

## ፪. ክለሳ ድርሳናት

ሰው እና ሰዋዊ ጉዳዮችን ትኩረታቸው ያደረጉ የምርምር መስኮች በጥናት ትኩረታቸው ተዛምዶ አላቸው፡፡ ይህ ተዛምዷቸውም በጥናት መስኮቹ መካከል ትብብርና ትስስር እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል (ቴዎድሮስ፣ ፳፻፩ ፡፡ ከእነዚህ መስኮች መካከል ደግሞ ፎክሎር እና ሃይማኖት ይጠቀሳሉ፡፡

### ፪.፩ ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ /Conceptual Framework/

ፎክሎር ሰዋዊ ጉዳዮችን የሚያጠና የሰብአዊ ሳይንስ የጥናት መስክ ነው፡፡ በውስጡም አራት ዋና ዋና ዘርፎችን የሚይዝ ሲሆን እነርሱም ሥነ ቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረ ሰባዊ ልማድ እና ሀገረ ሰባዊ ትውን ጥበባት ናቸው (Dorson 1972 እና ፈቃደ፣ ፲፱፻፺፩)፡፡ በፎክሎር መስክ ከሚዘወተሩ የጥናት አቅጣጫዎች[8] ውስጥ አንዱ የሃይማኖት (ሃይማኖታዊ) ፎክሎር ነው፡፡ በሃይማኖት ፎክሎር ሥር ሀገረ ሰባዊ ሃይማኖት እንደ አንድ ጉዳይ ከታየ ማኅበረሰቡ በተወሰኑ የሃይማኖት ስፍራዎች የሚከውናቸው

[8] የፎክሎር የጥናት አቅጣጫዎች ሲባል ፎኩን ወይም ሎሩን ማተኮሪያ በማድረግ ጥናት የሚደረግበት መንገድ ነው፡፡ ሎሩን መሠረት ያደረገ ጥናት ሥነ ቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ ወይም ትውን ጥበባት ከሚባሉት አንዱን መርጦ ማጥናት ይቻላል፡፡ ፎኩን መሠረት ያደረገው ጥናት ደግሞ የስራ ዘርፍን፣ የሀይማኖት ወይም የእምነት ተቋምን በመምረጥ በዚያ የሚከወኑ የፎክሎር ዘርፎች ማጥናት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሃይማኖታዊ ፎክሎር የፎክሎር ዘርፎች አከፋፈል አንዱ ሳይሆን በሥሩ የፎክሎር ዘርፎች የሚጠኑበት የጥናት አቅጣጫ ነው፡፡

ከበራዎችን ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት ሕይወቱ ውስጥ የሚከውናቸው ተግባራት ናቸው (Gustavsson፣ 2012፣ ገጽ 9) ። ሀገረ ሰባዊ ሃይማኖት ላይ የሚደረጉ ጥናቶች ትኩረታቸው ከዓመታዊ እንዲሁም ከሕይወት ሽግግር ከበራዎች ጋር የተያያዙ እምነቶችና ልማዶች እንዲሁም ተረኮችና ቁሳዊ መገለጫዎች ላይ መሆን ይገባዋል።

ፈቃደ (፲፱፻፺፩ ገጽ ፲፬) እንደሚሉት "የሀገረ ሰባዊ ሃይማኖት ምርምርም÷በልዩ ልዩ በዓላት ላይ፣ በመንደር፣ በቤተሰብ፣ በሃይማኖት (መስጊድ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ምኵራብ ወዘተ.) የሚካሄዱትን ክዋኔዎች፤ በልደት፣ በግርዘት፣ በክርስትና፣ በጋብቻ፣ በሞት እና እነዚህን በመሳሰሉ ክዋኔዎች ውስጥ የሚከሰቱ መስተጋብሮችን (interactions) ያጠናል"። ይህም ቀድሞ የቀረበውን ሐሳብ የሚያጠናክር ሆኖ በተለይ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚመለከት ነው። ሀገረ ሰባዊ ሃይማኖት፣ የሃይማኖት ፎክሎር አንዱ ክፍል ሲሆን፣ በአጠቃላይ የሃይማኖት ፎክሎር ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን አራቱን የፎክሎር ዘርፎች ትኩረቱ ያደርጋል። ይህ ጥናት ሃይማኖታዊ ፎክሎር ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ጥናቶች ለሃይማኖቱ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ መመርመር በሚል ሐሳብ መነሻነት ቃላዊ እና ቁሳዊ ባህል በተሰኙ የፎክሎር ዘርፎች ላይ ያተኮረ ነው።

ሥነ ቃል በመነገር በመተረክና በመዜም ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ የማኅበረሰብ ቃላዊ (አፋዊ) ሀብት ነው (ዘሪሁን፣ ፲፱፻፺፪)። በዋናነት አፋዊ ዝርው ትረካ እና ቃል ግጥም በተባሉ ንኡስ ዘርፎች ይከፈላል። የዚህ ጥናት ማተኮሪያዎችም ተረኮች ከአፋዊ ዝርው ትረካ እንዲሁም የተማጽኖና የምስጋና ግጥሞች ከቃል ግጥም ዘርፍ ሥር ይመደባሉ። በተጨማሪም ቁሳዊ ባህል ሊታዩ፣ ሊዳሰሱ፣ ሊቀመሱና ሊጨበጡ የሚችሉ ማኅበረሰቡ ዕውቀቱን ተጠቅሞ በአካባቢው የሚያገኛቸውን ተፈጥሮአዊ ቁሶች ወደ ባህል የቀየራቸውን ቁሳዊ መገለጫዎች ይመለከታል። በሥሩም አልባሳት ጌጣጌጦች እና መዋቢያዎች፣ ባህላዊ ምህንድስና፣ እደ ጥበባትና የእጅ ሥራዎች እና ምግቦችና መጠጦች ይካተታሉ (Dorson፣1972)።

በገዳማት ዙሪያ የሚነገሩ ቃል ተረኮች የገዳሙን ታሪክ፣ ቅድስና፣ ፈዋሽነት፣ ተዓምር ሠሪነት፣ ቃልኪዳን በገዳማውያኑና በሃይማኖቱ አማኞች ዘንድ ተቀባይነትንና ተከባሪነትን ማስፈን መቻልን የሚተርኩ ናቸው። እነዚህም ሥነ ቃል በተባለው የፎክሎር ዘርፍ ሥር ይጠናሉ። በሌላ በኩል ለአምልኮ መፈጸሚያነት የሚውሉ ዕቃዎች፣ የማምለኪያው ቤት አሠራር እና የሃይማኖቱ አገልጋዮች የሚለብሷቸው ልብሶች የፎክሎር ዘርፍ በሆነው በቁሳዊ ባህል ሥር ይጠናሉ። እነዚህም በሃይማኖት ተቋም እና በፎክሎር ዘርፍ መካከል ላለው ተዛምዶ አንድ ማሳያ ናቸው።

የሃይማኖት ፎክሎር ጥናት ፎክሎር እና ሃይማኖትን የሚያገናኝ ድልድል ነው። ሃይማኖት እና እምነት ደግሞ የፎክሎር ጥናት ትኩረት ናቸው (Phunoug፣ 2021)። ሃይማኖት የዕለት ተዕለት ሕይወትን ለሚቆጣጠር ልዕለ ሰብአዊ ኃይል አምልኮ ማቅረብ፣ ማመንና መታመን ነው። በመሆኑም "ሃይማኖት መንፈሳዊ/ ቅዱሳዊ መሠረት አላቸው ተብለው የሚተረኩ ሚቶችን በተግባር የሚያስፈጽም ተቋም ነው" በማለት በSariors (2007፣ ገጽ 8) ተገልጾአል። ከዚህ ሐሳብ በመነሳት ራሱን በአንድ ልዕለ ሰብ ሥር ያስጠጋውን ፎክ የልዕለ ሰቡን ተጋድሎ፣ ሕግጋት፣ አስተምህሮ፣ ጽድቅና ኵነኔ፣ ቅድስና፣ የሞትና ሕይወት እሳቤ የሚማረው እና የሚረዳው በተረክ አማካኝነት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ሃይማኖት የማኅበረሰቡ መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ዘልቆ ሲገባና የዕለት ተዕለት ሕይወት አንዱ አካል ሲሆን በተረክ አማካይነት ይገለጻል። የሃይማኖቱ አስተምህሮም ማስተማሪያ መንገድ ሆኖ የሚያገለግለው የሥነ ቃል አንዱ ክፍል የሆነው ተረክ ነው (Phunoug፣ 2021)። ስለዚህ ሃይማኖት የፎክ መንፈሳዊ ሕይወት ሲሆን የሚገለጸውም በተረክ ነው።

የቅዱሳን ተጋድሎ፣ ቃል ኪዳን፣ ቅዱስነት፣ አዳኝነት፣ አማላጅነት የሚነገርላቸው በተረክ አማካኝነት ሲሆን በአማኙ (የሃይማኖቱ ተከታይ) ዘንድ እንዲታወቁ፣ እንዲከበሩ ያደርጋል። ቃል ግጥም ስለ ቅዱሱ ሰው ምስጋና፣ ተማጽኖ/ልመና፣ አዳኝነት/ፈዋሽነት፣ ቅዱስነት፣ አማላጅነት የሚገለጽበት ሌላው የሥነ ቃል ዘውግ ነው። ስለዚህ ስለ ቅዱሱ ሰው፣ ገዳማትና አድባራት የሚነገሩ ተረኮችና ቃል ግጥሞች በሃይማኖቱ ውስጥ ያደረገውን ተጋድሎ የሚገልጹና በአማኙ ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነትና ተከባሪነት እንዲያገኝ የሚደርጉ ስነ ቃሎች ናቸው። በሌላ በኩል በሃይማኖት ፎክሎር ውስጥ ከሚጠኑ ቁሳዊ ባህሎች ንዋየ ቅድሳት ይገኛሉ። ሃይማኖታዊ ቁሶችን (ንዋየ ቅድሳትን) አስመልክቶ ሚሊዮን (፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፲፫-፲፬) ሲገልጽ «ንዋየ ቅድሳት ማለት ከተመረጡ የተመረጠ፣ ከተለዩ የተለየ፣ ስሙ ለዘለዓለም የሚኖርበት ምርጥ ዕቃ ማለት ነው። ለቤተ መቅደስ አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች የሚጠሩበት ስም ነው።» ንዋያተ ቅድሳቱ፣ አልባሳቱ፣ ሕንጻ ቤተክርስቲያኑ ለአገልግሎት ብቻ ተብለው የሚሠሩ አይደሉም። አሠራራቸው፣ የሚሠሩበት ጥሬ እቃ፣ መጠናቸው፣ ቅርጻቸው፣ የሚሠሩበት ቦታ፣ ብዛታቸው፣ ቀለማቸው ትእምርታዊ ነው። በሃይማኖቱ በኩል ይህንን ትርጓሜ ይያዙ እንጂ የፎክሎር መስክ በሆነው በቁሳዊ ባህል ጥናት ሲቃኙ ከማኅበረሰቡ የዕለት ተዕለት ሕይወትና እምነት ጋር ተያይዞ የሚሰጣቸው ትእምርት አላቸው።

ንዋየ ቅድሳት የሃይማኖቱን አምልኮዊ ክዋኔዎች ለመፈጸም የሚያገለግሉ የራሳቸው አሠራር፣ አገልግሎትና ተምሳሌት ያላቸው የሃይማኖቱ መገለጫዎች ናቸው። በመሆኑም በሃይማኖታዊ ፎክሎር የጥናት አቅጣጫ ምርምር የሚያካሂድ አጥኚ ጥሬ

መረጃዎቹን አንዱን የሃይማኖት ስፍራ በመምረጥና ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን አንዳች ውጤት ላይ እንዲደርስ ይጠበቃል። በዚህ ጥናትም በዚህ መንገድ የተጠኑት ጥናቶች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና የሃይማኖት ተቋም ያበረከቱት አስተዋጽኦ ተተንትኖ ቀርቧል።

## ፩.፬ የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፍ /Theoretical Framework/

ለዚህ ጥናት ማስኬጃነት የተመረጠው የንድፈሀሳብ ማዕቀፍ ነው። የዚህ ንድፈ ሐሳብ ዋና ማጠንጠኛ ሐሳብ ማንኛውም በማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኝ "ሎር" አንዳች አገልግሎት ወይም ፋይዳ ይኖረዋል የሚል ነው። በዚህ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች እሳቤ አገልግሎት ወይም ጠቀሜታ የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ምንነት Szonyi (2018፣ ገጽ 42) (Kisdi, 2012፣ ገጽ 116; Radcliffe-Brown, 2004፣ ገጽ 21, 157, 173) ን በመጥቀስ የሚከተለውን ብያኔ አቅርባለች። "The function… implies that a certain social practice or attitude plays a role in sustaining the social continuity throughout its function". በቀረበው ሐሳብ መሠረት አንድ ማኅበራዊ ድርጊት ወይም ሁኔታ ባለው ጠቀሜታ ወይም በሚያበረክተው አስተዋጽኦ የማኅበረሰቡ ቀጣይነት ተጠብቆ እንዲቀጥል ምክንያት ይሆናል። ይህ ንድፈ ሐሳብም በፎክሎር እና በባህል ጥናቶች በስፋት አገልግሎት ላይ የሚውል መሆኑን በKamppinen (2014፣ p. 7) ተገልጾአል። በዚህ ጥናትም ሃይማኖታዊ ፎክሎር ላይ የተጠኑት ጥናቶች የሃይማኖት ተቋሙን ገጽታ በማሳየት፣ ለማኅበራዊ ትስስርና የሃይማኖት ቦታዎቹን የቱሪዝም ተደራሽ በማድረግ ረገድ ያላቸውን አበርክቶ ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል። በተጨማሪም በሃይማኖታዊ ፎክሎር ላይ የተጠኑ ጥናቶች አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማትና ቅዱሳት ቦታዎችን ለሃይማኖቱ ባለቤትም ሆነ ከሃይማኖቱ ውጪ ላለው የማኅበረሰብ ክፍል በማስተዋወቅ ረገድ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መመርመር በመሆኑ ይህ የንድፈሀሳብ ማሕቀፍ ተግባራዊ ተደርጓል

## ፩.፭. የጥናቱ ሥነ ዘዴ

የፎክሎር ጥናቶች ሃይማኖትን በማስተዋወቅ እና ቃላዊና ቁሳዊ መገለጫዎችን ቀርሶ በማቆየት ረገድ ያላቸውን ሚና ማሳየት ላይ ያተኮረው ይህ ጥናት አይነታዊ የአጠናን መንገድን የተከተለ ነው። መረጃዎች የተሰበሰቡት በመዛግብት ፍተሻ ዘዴ ነው። ለጥናቱ የተመረጡት መስኮች በአመቺ የናሙና ዘዴ የተመረጡ ሲሆን መረጃዎቹንም ለመምረጥ ዓላማ ተኮር የናሙና አይነት ተግባራዊ ተደርጓል። የተቋማት ምርጫን በተመለከተ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሃይማኖት ተቋምና እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሥር የሚገኘው የፎክሎር የጥናት መስክ መረጃዎችን በቅርበት ለማግኘት የሚያስችሉ በመሆናቸው ተመርጠዋል:: በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ዲግሪ የተሠሩ የሃይማኖት ፎክሎር ጥናቶችን በመለየት፣ እንዲሁም የሃይማኖት ፎክሎርን ጉዳያቸው ካደረጉት ውስጥ በሥነ ቃልና በቁሳዊ ባህል ላይ የተጠኑትን የጥናቱን ዓላማ መሠረት በማድረግ በመምረጥ ነው::

በአጠቃላይ በሃይማኖት ፎክሎር ላይ የተጠኑት ጥናቶች ፳፱ ሲሆኑ ለዚህ ጥናት በዓላማ ተኮር ናሙና የተመረጡት ፲፪ ናቸው:: እነዚህም በመጀመሪያ ዲግሪ ሦስት እና በሁለተኛ ዲግሪ ዘጠኝ ናቸው:: ጥናቶቹም ሥነ ቃል፣ ቁሳዊ ባህል ነጥለው እንዲሁም ሥነ ቃልና ቁሳዊ ባህልን አጣምረው ያጠኑ በሚል በሦስት ጎራ ከተከፈሉ በኋላ የትኛው ሃይማኖታዊ ቦታ፣ ምን ጉዳይ ትኩረት ተሰጠው? አበርክቶውስ ከምን አንጻር ነው? የሚሉ ማጠንጠኛ ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ በዘመን ቅደም ተከተል ከቀድሞ ወደ አሁን ተደራጅተው ገለጻ የመተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ተተንትነው ቀርበዋል::

## ፫. የመረጃ አቅርቦትና ትንተና

በዚህ ጥናት ለትንተና የተመረጡት የመመረቂያ ጥናቶች በጥናቱ ዓላማ መሠረት በንኡስ ምዕራፎችና ክፍሎች ተመድበው እንደሚከተለው ተተንትነዋል::

### ፫.፩ በሃይማኖት ፎክሎር ላይ የተካሄዱ የተመረጡ ጥናቶች

በዚህ ጥናት ለትንተና የተመረጡት መመረቂያ ጥናቶች የሚከተሉት ናቸው:: በመጀመሪያ ዲግሪ የቀረቡት ጥናቶች በዐቢይ ፍትሕ ዐወቅ (፲፱፻፷፫)፣ በስመኘው አራጌ (፲፱፻፹፬) እና በአንተነህ ደሴ (፳፩) የቀረቡ ሦስት ጥናቶች ናቸው:: ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡት ደግሞ በተናኘ አበበ፡ (፲፱፻፺፱) ፣ በፍሬ ሕይወት ባዩ (፳፻) ፣ በምሕረት ተስፋዬ (፳፻፫) ፣በተስፋዬ ተገኘ (፳፻፫)፣ በቴዎድሮስ ይበልጣል (፳፻፭)፣ በፍጹም ኩራባቸው (፳፻፮)፣ በወንድወሰን ሞላ (፳፻፯)፣ በዮሴፍ ቦኪ (፳፻፯ እና በመሪማ መሐመድ (፳፻፱) የቀረቡ ፱ ጥናቶች ናቸው:: በጥናቱ ዓላማ መሠረት በጥናቶቹ ተተኳሪ የሆኑት የፎክሎር ዘርፎችን እና አበርክቶአቸውን መከፋፈያ በማድረግ ትንተናው እንደሚከተለው ቀርቧል::

#### ፫.፩.፩. በቃል ተረክ እና ቃል ግጥም ላይ የተጠኑ ጥናቶች

በዚህ ርእስ ሥር የተቃኙት ጥናቶች ለጥናት በመረጡት አካባቢ /ቅዱስ ስፍራ/ ቃላዊ ሃብቶች ላይ አተኩረው ያጠኑ ናቸው:: በተቃኙት ጥናቶች ቀድሞ

የሚመጣውና ጎልቶ የሚታየው የሚጠናው አካባቢ ወይም ቤተ ክርስቲያን መጠሪያ ነው። በመሆኑም የጥናቶቹ አበርክቶ የሚያጠኑትን ስፍራ በማስተዋወቅ ይጀምራል። ለዚህ ማሳያ የሚሆኑትን እና በጥናቶቹ የተመረጡ ስፍራዎችን የጠቀሱ ጥናቶችና የተጠቀሱት ስሞችም ደብረወርቅ ማርያም ገዳም (ቴዎድሮስ፣ ፳፻፭)፣ ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም፣ የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም (ዮሴፍ፣ ፳፻፯) የሚሉት ናቸው። ጥናቶቹ ለጥናታቸው የተመረጧቸውን ገዳማት እና አድባራት በርእሳቸው በመጥቀስ አንባቢ ከርእሱ ጀምሮ ስለጉዳዩ ዕውቅና እንዲኖረው የሚያደረጉ ጥናቶች ናቸው።

በዚህ ርእስ ሥር የተቃኙት ሌሎቹ ጥናቶች ደግሞ በቀጥታ የሚጠናውን ገዳም ወይም የቤተ ክርስቲያኑን ስም ከመጥቀስ ይልቅ ገዳሙ/ቤተክርስቲያኑ/ በሚገኝበት አካባቢ መጠሪያ የሚጀምሩ ናቸው። በፍጹም (፳፻፯) የቀረበውን ጥናት ብንመለከት በጥናቱ ርእስ የተመረጠው ቅዱስ ስፍራ ከአንድ በላይ በመሆኑ ገዳማቱ እና አድባራቱ የሚገኙበትን ስፍራ ለአቅጣጫ መጠቆሚያነት ተጠቅሟል። በመሆኑም አንባቢ በቅድሚያ ዝዋይ የሚል አካባቢን በአካባቢውም ደሴቶች እንደሚገኙ እና ደሴቶቹ ላይም ገዳማትና አድባራት እንዳሉ ርእሱን በማየት ቅድመ ዕውቅና እንዲያገኝ መረጃ ይሰጣል። በዚህ ረገድ የተጠኑት ጥናቶች በልዩ ልዩ አካባቢዎች የሚገኙ ገዳማትን ወይም አድባራትን በስም በመጥቀስ በማስተዋወቅ ረገድ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በተጨማሪም ጥናቶቹ በርእሳቸው ላይ የሚያጠኑትን ጉዳይ የሚጠቅሱ በመሆናቸው ስለሚጠናው ቅዱስ ስፍራ ምን ጉዳይን ለአንባቢ እንደሚነግሩ ወይም እንደሚገልጹ መረዳት ይቻላል። ቀደም ሲል የተጠቀሱት ጥናቶች የተመረጠውን ስፍራ በሚመለከት አመሠራረቱን ወይም አጠቃላይ ሃይማኖታዊ ስፍራነቱን በሚመለከት የሚነገሩ ቃል ተረኮችን ማጥናት ላይ ያተኮሩ ናቸው። ስለሆነም አንባቢ ከተመረጡት ገዳማት ወይም አድባራት የስም ዕውቅና በተጨማሪ አመሠራረታቸውን፣ የቤተ ክርስቲያኑን አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጹ ቃላዊ ተረኮችን በጥናቶቹ እንደሚያገኝ ያስችሉታል። በዚህ ርእስ ሥር ከተካተቱት ጥናቶች መካከል ከቀደሙት በተለየ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓልን መሠረት በማድረግ ቃል ግጥሞችን ትኩረቱ ያደረገ ጥናት እናገኛለን። ይህ

ጥናት በስመኘው (፲፱፻፹፬) የቀረበ ሲሆን በጥናቱ ጾመ ፍልሰታ እና የላሊበላ ንግሥ የሚባሉ ሃይማኖታዊ መሠረት ያላቸው ጉዳዮች ተቃኝተዋል፡፡ በእነዚህ በዓላት ላይ የሚከወኑ ቃል ግጥሞችም የዚህ ጥናት ጉዳዮች ናቸው፡፡

### ፫.፩.፪. ቁሳዊ ባህል ላይ ያተኮሩ ጥናቶች

በመግቢያው ክፍል ለመግለጽ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚገኙ ቤተ መጻሕፍት በተደረገ ዳሰሳ በሃይማኖታዊ ፎክሎር ዘርፍ ላይ የቀረበው የመጀመሪያው ጥናት (ዐቢይ፣ ፲፱፻፷፫) በዚህ ክፍል የሚካተት ነው፡፡ ለትንተና በተመረጡት ጥናቶች ላይ በተደረገ ፍተሻ በዚህ ክፍል የሚገኙ ጥናቶች በአንተነህ (፳፻፩) ከቀረበው ጥናት በስተቀር በሥነ ቃል ክፍል እንደ ቀረቡት ጥናቶች የአንድን ገዳም ስም ከመጥቀስ ይልቅ የሃይማኖት ተቋምን ስም በመጥቀስ የሚጀምሩ ናቸው፡፡ እነዚህም የዐቢይ እና የፍሬ ሕይወት (፳፻) ጥናቶች ሲሆኑ ቁሳዊ ባህልን ለብቻ ነጥለው ያጠኑ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች ውስጥ የጥናቱ ትኩረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ የምናገኘው በፍሬሕይወት ጥናት ነው፡፡ አጥኚዋም በኢትዮጵያ ከሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን መምረጧ በጥናቷ ርእስ ላይ ተገልጾ ይገኛል፡፡

እነዚህም ጥናቶች በቀደመው ክፍል እንደቀረቡት ጥናቶች ሁሉ የሚያጠኑትን ጉዳይ በርእሳቸው ጠቅሰው እናገኛለን፡፡ በዚህ መሠረት በሁለቱም ጥናቶች ንዋየ ቅድሳት ዋና ጉዳዮች ሲሆኑ በዐቢይ ጥናት የሃይማኖት ፎክሎር አንዱ ጉዳይ የሆነው የቁሳዊ ባህል ዘርፍ (የሃይማኖት አልባሳት እና ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን) በተጨማሪነት የጥናቱ ትኩረት ሆነው ቀርበዋል፡፡ እነዚህም ጥናቶች የሚያጠኑትን የሃይማኖት ተቋም ገና በርእሳቸው ላይ መግለጻቸው አንባቢ የትኛው የሃይማኖት ተቋም ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ ተቋሙን በማስተዋወቅ ረገድም ድርሻ አላቸው፡፡ እንዲሁም በርእሳቸው ላይ ንዋየ ቅድሳት የሚለው ቃል መጠቀሱ አንባቢ ሃይማኖታዊ ቁሶችን በጥናቱ ሊያገኝ እንደሚችል ዕውቅና በመስጠት ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አለ፡፡

በዚህ ክፍል ሌላው የሚገኘው ጥናት የአንተነህ (፳፻፩) ጥናት ነው። በዚህ ጥናት ርእስ ላይ ዳባት ገብርኤል የሚባል ቤተ ክርስቲያን ስም ተጠቅሶ ይገኛል። በመሆኑም ከላይ ከቀረቡት ሁለት ጥናቶች በተለየ በስነቃል ጥናቶች ክፍል እንዳየነው የሚጠናውን ቤተ ክርስቲያን ስም መጥቀሱ አንባቢ ገና በርእሱ ስለሚጠናው ቅዱስ ስፍራ የስም ዕውቅና እንዲኖረው አድርጓል። በተጨማሪም ጥናቱ ቁሳዊ ባህልን ለይቶ ያጠና ሲሆን በቤተ መዘክር የሚገኙ ቅዱሳት ቁሶችን ከአጫጭር መግለጫ ጋር ማቅረብን ዋና ጉዳዩ አድርጎ የተነሣ ጥናት ነው። ይህም የተመረጠውን ቤተ ክርስቲያን ለአንባቢ በማስተዋወቅ ረገድ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ምክንያት ሆኗል።

## ፫.፩.፫. ሥነ ቃል (ቃል ተረኮች) እና ቁሳዊ ባህሎችን አጣምረው የተጠኑ ጥናቶች

በዚህ ክፍል የተመደቡት ቃል ተረኮችንና ቁሳዊ ባህልን አጣምረው ያጠኑ ሦስት ጥናቶች ናቸው። እነዚህ ጥናቶች በሥነ ቃል ጥናቶች ክፍል እንዳየነው በርእሳቸው ላይ የሚያጠኑዋቸውን ገዳማት ስም በመግለጽ ይጀምራሉ። ገዳማቱም የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ አንድነት ገዳም (ተስፋዬ፣፳፻፫)፣ ጣናቂርቆስ አንድነት ገዳም (ምህረት፣ ፳፻፫) እና የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም (መሪማ፣፳፻፱) ናቸው። በመሆኑም እነዚህ ጥናቶች በርእሳቸው የሚያጠኑትን ቅዱስ ስፍራ ስም በመጥቀሳቸው በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ገዳማትን በስም በማስተዋወቅ አንባቢ ጥናቶቹን እንዲያነብ እና ስለ ገዳማቱም ዕውቀት እንዲያገኝ ፍንጭ በመስጠት ረገድ አስተዋጽኦ አላቸው።

በሦስት ንኡስ ክፍሎች የቀረቡት የሃይማኖታዊ ፎክሎር ጥናቶች ዓላማዎቻቸው በመረጧቸው ቅዱሳት መካናት የሚገኙ ቃላዊ እንዲሁም ቁሳዊ መገለጫዎች ላይ ትኩረታቸውን በማድረግ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ለማጥናት የሞከሩ ናቸው። የጥናት ዳራ፣ ክለሳ ድርሳናት እና ትንተና ባቀርቡባቸው ክፍሎች ደግሞ የተቋሙን ታሪክ የመረጧቸውን መካናት አመሠራረት ታሪክ፣ ቃል ተረኮች፣ቃል ግጥሞች እና ንዋየ ቅድሳት ያላቸውን አገልግሎት መግለጽ ላይ ትኩረት አድርገዋል። በዚህ ጥናት በቀጣይ ክፍል ጥናቶቹ በየርእሳቸው ሃይማኖታዊ ስፍራዎችን በማስተዋወቅ ረገድ ካበረከቱት አስተዋጽኦ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሃይማኖት ተቋምን በማስተዋወቅ ረገድ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከየጥናቶቹ የተለያዩ ክፍሎች ማሳያዎችን በማቅረብ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## ፩. የጥናት ሥራዎቹ ለሃይማኖት ተቋሙ ያበረከቱት አስተዋጽኦ

በሃይማኖት ፎክሎር የሚቀርቡ ጥናቶች ትኩረታቸው አንዱን ወይም ሁለቱን የፎክሎር ዘርፍ መሠረት በማድረግ ከሃይማኖታዊ ትርጉም ወይም አገልግሎታቸው ጎን ለጎን ያላቸውን ባህላዊ መገለጫ ማሳየት ነው። በዚህ ሂደትም የሚያጠኑትን የሃይማኖት ተቋም አመሰራረት ታሪክ፣ የተቀደሱ ስፍራዎችን፣ በስፍራዎቹ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ባህሎችን መረጃ አድርገው ያቀርባሉ። ይህ ደግሞ የዚህ ጥናት አቅራቢዎች ዓላማ አድርገን በተካሄደበት መንገድ የሃይማኖት ተቋሙን በማስተዋወቅ ረገድ የራሳቸው አበርክቶ እንዲኖራቸው ምክንያት ይሆናል። እነዚህ ገዳማት፣ አድባራትና እና አብያተ ክርስቲያናት የሀገር ሀብት በመሆናቸውም በዚህ አጋጣሚ የጥናት አካል ተደርገው ሲቀርቡ በሃይማኖቱ ውስጥ ያለም ሆነ ከሃይማኖቱ ውጭ ያለ አካል (አንባቢ) እነዚህን ሀገራዊ ሀብቶች እንዲያውቅ በማድረግ ረገድ መነሣሣትን ይፈጥራሉ። አካባቢውን የማየት፣ የመጎብኘት ፍላጎትም እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፤ጉልህ ፋይዳም ይኖራቸዋል።

በመረጃነት የተመረጡት ጥናቶች በርእሶቻቸው የሃይማኖት ሥፍራዎችን በማስተዋወቅ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በተጨማሪ ለጥናት የመረጧቸው ቃል ተረኮች፣ ቃል ግጥሞችም ሆኑ ቁሳዊ ባህሎች ያላቸውን ጠቀሜታ ለትንተና በመከፋፈያነት ተጠቅመዋል። ለትንተናውም ይረዳቸው ዘንድ አብዛኞቹ ጠቀሜታዊ ንድፈ ሐሳብን ተጠቅመዋል (ቴዎድሮስ፣ ፳፻፫፤ ፍጹም፣ ፳፻፮፤ ዮሴፍ፣ ፳፻፯፤ ወንድወሰን ፳፻፯፤ መሪማ፣ ፳፻፱) ። ቃል ተረክን[9] ጉዳያቸው አድርገው ባጠኑት ጥናቶች የትንተና ክፍል በገዳማት ዙሪያ የሚነገሩ ቃል ተረኮች የገዳሙን ታሪክ፣ ቅድስና፣ ፈዋሽነት፣ ተአምር ሠሪነት፣ ቃልኪዳን በገዳማውያኑና በሃይማኖቱ አማኞች ዘንድ ተቀባይነትንና ተከባሪነትን ማስፈን በሚሉ ርእሶች ማስረጃዎችን በመስጠት ትንታኔያቸውን አቅርበዋል።

### ፩.፩ በተረኮች ላይ የቀረቡ ጥናቶች አስተዋጽኦ ቅኝት

#### ሀ. የገዳሙን ጥንታዊነት የመዘከር ፋይዳ

በገዳማት ላይ በተጠኑት ጥናቶች ውስጥ የተመረጠው ገዳም ጥንታዊና ታሪካዊ መሆኑን የሚያሳዩ ተረኮች ቀርበው እናገኛለን። ቃል ተረኮቹ ስለ ጥንታዊነቱ ትንቢት የተነገረለት መሆኑን በመግለጽ እንዲሁም ከሌሎች ገዳማት ጋር በማነጻጸር ለጥናት የተመረጠውን ገዳም ጥንታዊነትና ቀዳማይነት ይሰብካሉ። ከነዚህ መካከል በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ

[9] ቃል ተረክን ጉዳያቸው ያደረጉ ጥናቶች ቃል ተረክን ለይተው ያጠኑ አልያም ቃል ተረክና ቁሳዊ ባህልን አጣምረው ያጠኑ ናቸው።

ሃይማኖት ገዳም ላይ የተሠራው የዮሴፍ ጥናት አንዱ ነው:: በጥናቱ "የገዳሙን ጥንታዊነት የመዘከር ፋይዳ" በሚለው የትንተናው ክፍል የሚከተለው ሐሳብ ቀርቦ እናገኛለን:: "እመቤታችን በስደቷ ጊዜ ልጇን ይዛ በደመና ሳሉ ልጇን "ይቺ ቦታ ማናት?" ብትለው፣ "ሀሐሓበበሀደደነነነመበኂለኛው ዘመን በንጽህናውና በቅድስናው የጸና ደግ አባት የሚነሳባት ቦታ ናት" አላት:: በዋሻዋም አረፉባት" (ዮሴፍ፣ ፳፻፪፣ ገጽ ፶፪) :: እንደ አጥኚው ገለጻ ይህ ተረክ ገዳሙ ከልደተ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ያለ መሆኑን ለማሳወቅ የቀረበ ነው:: ገዳሙ አቡነ ተክለሃይማኖት ከመነሣታቸው በፊት በአምላክ ልቡና የታሰበ እንደሆነና አማኙም ጥንታዊነቱን እንዲቀበል የማድረግ ተግባር እንዳለው ተገልጿል::

የገዳሙን ጥንታዊነት ለማሳየት በተጨማሪነት የቀረበው ተረክ እንዲህ ይላል፤ "መላእክትም ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ከጎኑ የፈሰሰውን ደም ረጭተዋል:: ደሙ ባረፈበት ቦታ ላይ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን፣ ገዳም ይገነባል:: የተክለ ሃይማኖት ገዳምም የተገነባው እንደነ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ግሸን፣ ዝቋላ ደሙ ዐርፎበት ነው" (ዮሴፍ፣፳፻፪፣ ገጽ ፶፫):: አጥኚው የዚህን ተረክ መልእክት በተመለከተ ሲገልጽ ገዳሙ በቅዱስ አባት ወይም ፈጣሪ ደም የተባረከ መሆኑን እንዲሁም ገና ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል እንደ ተመረጠ በማገናዘብ ጥንታዊነቱን ለማጉላት የቀረበ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ አስፍሯል::

ጥንታዊነት በተረክ አማካይነት የቀረበበት ሌላኛው ጥናት የጻድቃኔ ማርያም ገዳም ላይ የተጠናው ነው:: ገዳሟ በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን የተመሠረተች ጥንታዊት መሆኗን የሚያመለክት ተረክ በወንደሰን (፳፻፪፣ ገጽ ፵፩) ተጠቅሶ እናገኛለን::

> እመቤታችን በራእይ ተገልጻ ቤተ ክርስቲያንን የሚያወድም፣ ካህናትንም የሚያጠፋ አሕዛብ መጥቷልና ንዋየ ቅድሳትን፣ ተራራውን ቆፍረህ፣ ገደሉን ጠርበህ ከዓለም ሰውር ብላ ነገረቻቸው:: ከዚያ በኋላ ንጉሡ ንዋየ ቅድሳቱን ሰውረው አሁን የዘርዐ-ያዕቆብ ዋሻ ተብላ የምትጠራው ውስጥ በመግባት ሱባኤ ያዙ:: 'እመቤቴ ሆይ አሁንስ መቼ ነው ከዚህ ዋሻ ውስጥ የማወጣሽ?' ብለው ቢጠይቋት አይ እኔ ከዚህ አልወጣም እንዳንተ የነቃ፣ የበቃ ጻድቅ ይየኝ፤ አላቻቸው:: የገዳሙም ስም ጻድቃኔ ማርያም ተባለ::

ይህ ተረክ ጻድቃኔ ማርያም ገዳም ቀድሞም ትንቢት የተነገረላት ጥንታዊት ገዳም መሆኗን የማሳየት ፋይዳ አለው::

## ለ. የገዳሙን ቅድስና የመዘከር ፋይዳ

ቅድስና የተለየ፣ የተመረጠ፣ ንጹህ ክቡር ማለት ነው። ለጥናት በተመረጡት ገዳማት ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች የገዳማቱን ቅዱስ መሆን የሚያጎሉ ናቸው። ቃል ተረኮቹ ቅዱስ መሆንን ያሳዩበት መንገድ በቅዱስ ሰው የተመረጠ መሆኑን በማሳየት፣ ቃልኪዳን ያለው መሆኑን በመግለጽ እንዲሁም የተለያዩ ገቢረ ተዓምራትን በማሳየት የተመረጠና የተቀደሰ መሆኑን በመግለጽ ነው።

በዮሴፍ ጥናት የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ቅዱስ መሆኑን የሚያሳዩ ቃል ተረኮች ቀርበዋል። ከነዚህም መካከል አንዱ፣ "አቡነ ሀብተማርያም የሠርክ ጸሎታቸው ስሞት ኢየሩሳሌም ልቀብር የሚል ነበር። ይህን የሰሙ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ልጄ በቦታዬ ተቀበር ቢሏቸው አልስማማም አሉ" (ዮሴፍ፣፳፻፯፣ገጽ ፶፱) ። ይላል። ተረኩ ቀጥሎም "በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሀብተ ማርያም ኢየሩሳሌምንና ደብረ ሊባኖስን በሁለት እጆቹ ዘርግቶ ተመሳሳይ አድርጎ አሳያቸውና ምረጥ አላቸው፤ እጃቸውም ከደብረ ሊባኖስ አረፈ። መቃብራቸውም በዚያው ተፈጸመ" (ዮሴፍ፣ ፳፻፯) ። ይህ ተረክ በጥናቱ እንደ ተገለጸው፣ የደብረሊባኖስ ገዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ከተቀበረበት የኢየሩሳሌም ገዳም ጋር ተመሳሳይ የሆነ ክብርና ቅድስና እንዳለው የማሳየት ተግባር አለው። ይህም የሃይማኖቱ አማኝ ኢየሩሳሌም በመሄድ የሚያገኘውን ጸጋና በረከት ደብረ ሊባኖስም ቢሄድ እንደሚሰጠው ለማድረግ የቀረበ ነው። ይህ ደግሞ ለገዳማውያኑ የቦታውን ቅድስና አጉልቶ ያሳያል። ለሌሎችም ቦታው የተቀደሰ እና የበረከት ስፍራ እንደሆነ ማሳያ ነው።

የደብረ ሊባኖስ ገዳም የተቀደሰ መሆኑን የሚገልጸው ሌላኛው ተረክ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቃልኪዳን ሲገባላቸው ልጆችህን እንደ ምድር አሸዋ አበዛቸዋለሁ ሲላቸው ምን ሠርተው? ምን በልተው? ቢሉት እርሱም እንኳን በአንተ ስም እኔን የሚለምኑ ይቅርና ምድራቱም ጾም አታድርም ይላቸዋል" (ዝኒ ከማሁ) የሚል ነው። ይህ ተረክ ለቅዱሳኑ ቃልኪዳን የሚሰጣቸው የተጋደሉለት ቅዱስ አምላክ እንደሆነ እና ቃሉም እንደሚፈጸም ያመለክታል። በደብረ ሊባኖስም የሚኖሩ ሕዝቦችም የሠሩት ሥራ ተባርኮላቸው ውጤታማ እንደሚሆኑ በማሳየት እምነታቸውን የማጽናት፣ ቦታውም የተመረጠና ቅዱስ መሆኑን የማሳየት ተግባር እንዳለው በጥናቱ ተገልጿል።

ጻድቃኔ ማርያም ገዳም ላይ በተጠናው ጥናት ውስጥም ገዳሙ ቅዱስ መሆኑን የሚያሳዩ ተረኮች ቀርበዋል። ከእነዚህም ገዳሙ ቃልኪዳን የተገባለት ስፍራ መሆኑ የሚያሳየው ተረክ አንዱ ማሳያ ነው። "ቅድስት ድንግል ማርያም አጼ ዘርዐ ያቆብን በህልም ንዋየ

ቅድሳቱን ከግራኝ አህመድ ጦርነት ለማዳን በዋሻ እንዲሰውር አድርጋዋለች" (ወንደሰን፣ ፳፻፯፣ ገጽ ፶) ። በጥናቱ እንደ ቀረበው ይህ ተረክ ገዳሙ ቃልኪዳን የተገባለት ቅዱስ ቦታ መሆኑን በማጉላት አማኞች ከቃልኪዳኑ በረከት ለማግኘት ሲሉ ወደ ገዳሙ እንዲጓዙና የተለየ ቅዱስ ቦታ መሆኑ እንዲታወቅ የማድረግ ፋይዳ አለው። ቦታውም በቅድስት ድንግል ማርያም የተመረጠ ቅዱስ ስፍራ መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም በተረክ አማካይነት የጻድቃኔ ማርያም ገዳም የወደፊት ዕጣ ፈንታን የመግለጽ ኃይል ያለው መሆኑ ተገልጿል። ለአብነት አጥኚው የሰሜን ሸዋ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ኤፍሬም ልጅ እያሉ በገዳሙ ሲጸልዩ ትልቅ ዛፍ እያሳየቻቸው ይህ የሥላሴ ወንበር ነው እንዳለቻቸው የሚገልጽ መረጃ ከገዳሙ መጽሔት ላይ ቀርቦ ማግኘቱን ጽፏል (ዝኒ ከማሁ)። ተረኩም የሰውን ልጅ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የማሳየት፣ ቀድሞ የማሳወቅ ኃይል ያለበት በመሆኑ የቦታውን ቅዱስነት የማጽናት ተግባር እንዳለው ተገልጿል።

### ሐ. የገዳሙን ክብርና ህልውና የማስጠበቅ ፋይዳ

የገዳም ክብር ከጥንታዊነት፣ ከታሪካዊነትና ከቅድስና ጋር ሊዛነቅ ይችላል። ይሁን እንጂ አጥኝዎቹ ተረኮቹን ከተነተኑበት ዐውድ አንጻር ሲፈተሹ የገዳሙን ታላቅነት የማሳየት ፋይዳም እንዳላቸው ያሳያሉ። የገዳማቱ ክብርና ሉዓላዊነት (ደህንነት) የሚጠበቀው በሰዎች ብቻ ሳይሆን በቅዱሳንም ጭምር እንደሆነ በማሳየት አማኙ ከሃይማኖቱ ሕግ ሲያፈነግጥ የሚደርስበትን ቅጣት በማሳየት የገዳሙን ክብርና ሉዓላዊነት የማሳወቅ ተግባር አላቸው።

በደብረ ሊባኖስ ገዳም በተጠናው ጥናት እንደ ተገለጸው ገዳሙ ታላቅ ገዳም ስለ ሆነ የትኛውም የአገልግሎት ዓይነት (ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ኪዳን፣ ማኅሌት፣ ሠርክ ጉባኤ) ከዓመት እስከ ዓመት አይታጎልም። "አባ ሊባኖስ የሚባሉ የእስክንድርያ/ግብጽ ጳጳስ ለልጆቻቸው ግብጻውያን ደብረ ሊባኖስ የሚጸለየው ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር እንደሚደርስ ነግረው ቅዳሴ ስትገቡም ሆነ ስትወጡ ከደብረ ሊባኖሶቹ ሰዓት ጋር ተመሳሳይ ይሁን ይሏቸዋል" (ዮሴፍ ፳፻፯፣ ገጽ ፸፩) ። ይህ ተረክ በጥናቱ እንደተገለጸው የደብረ ሊባኖስ ገዳምና በውስጡ የሚከናወኑ ሥርዓቶች ለሌሎች አብነት መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ይህ ደግሞ ገዳሙ ታዋቂና ቀዳሚ መሆኑን ለማጠየቅ የቀረበ ነው። ይህን ጥናት የሚያነብ አንባቢም ከጥናቱ ባገኘው የንባብ መረጃ ገዳሙ ታላቅ እንደሆነ መረጃ ማግኘት ያስችለዋል።

ፍጹም ባቀረበው ጥናት ውስጥም እንዲሁ የገዳማትን እና የአድባራትን ክብርና ታላቅነት የሚገልጡ ተረኮች በመረጃነት ቀርበዋል። በዝዋይ ሐይቅ ላይ በሚገኙ አምስቱ ደስያት

ገዳማትና አድባራት የቦታውን ክብርንና ሉዓላዊነት ለማሳወቅ ከሚተረኩ ተረኮች ደብረ ሲና ደብርን የተመለከተውን አጥኚው እንዲህ አቅርቧል። ይህም "የደብረ ሲና ደብር ከሳር የተከደነ ስለ ነበር በመቆየቱ ሳሩ ስለ በሰበሰ ዝናብ ማስገባት ጀምሯል። ዝናቡም ንዋየ ቅድሳቱን ማበላሸት ጀምራል። ሕዝቡ ግን ትኩረት አልሰጠውም። እግዚአብሔርም ቁጣውን ሲያሳይ ከሰማይ እሳት ወርዶ ሳሩን ብቻ አቃጥሎ ይጠፋል" (ፍፁም፣ ፳፻፮፣ ገጽ ፹፮) ።

በዚህ ተረክ ማኅበረሰቡ እግዚአብሔር ክብሩን የሚገልጽበት ስፍራ መሆኑን አውቀው የሃይማኖቱ ተከታዮች እንዲጠብቁትና እንዲያከብሩት የማድረግ ተግባር አለው። በተጨማሪ በዚሁ ጥናት የቀረበው ሌላው ተረክ፣ "በጥምቀት በዓል ሕዝቡ ሳይሰበሰብ ታቦቱን ይዘው ሲሄዱ አንድ ምእመን ታቦት የያዘውን ቄም ሕዝቡ ይሰብሰብ ይላል። በዚህ ጊዜ ታቦቱን የያዘው ቄስ አልቆምም እንሂድ ሲል ምእመኑ አላስኬድም ይላል። ለታቦቱ ጥላ የሚያጠላው ቄስ አላስኬድ ባለው ሰው ላይ ቢያጠላበት ልብሱ በእሳት ተቃጠለ" (ፍጹም፣ ፳፻፮፣ ገጽ ፹፯)። በዚህ ተረክ አማካይነት የገዳማቱና አድባራቱን ክብርና ሉዓላዊነት እግዚአብሔር በቃልኪዳኑ ታቦት እንደሚጠብቀው የማሳየት ተግባር አለው።

በዚሁ ንኡስ ርእስ ሥር በደብረወርቅ ማርያም ገዳም የሚነገር ተረክን መጥቀስ ይቻላል። በዚሁ ገዳም ላይ በተካሄደው ጥናት እንደቀረበው በደርግ ዘመነ መንግሥት ዕቃ ቤቱን ሰብረው በመግባት ውድ የሆኑ ዕቃዎችን ወደ ወታደራዊ ካምፕ በወሰዱ ጊዜ የገዳሚን ልዕልና የሚያስጠብቅና የሚጠብቅ ልዕለ ተፈጥሮ እንደሆነ የሚያሳይ ተረክ ቀርቧል። ይኸውም "ከገዳሚ ሁለት የብራና መጻሕፍት፣ ሦስት ቁሮች እና በርካታ ስጋጃ ምንጣፎችን የደርግ ወታደሮች ወስደው ነበር (ቴዎድሮስ፣ ፳፻፫፣ ገጽ ፺)። ስጋጃውን ቢተኙበት የጤና እክል ስለገጠማቸው ለገዳሚ መመለሳቸውን እንዲሁም የብራና መጻሕፍቱንና የራስ ቁሮቹን በሂሊኮፍተር ጭነው ሊወስዱት ቢፈልጉ ሄሊኮፍተሩ አልንቀሳቀስ ብሎ ቢያስቸግራቸው ይህንኑ ፈርተው ለገዳሙ መመለሳቸውን የሚገልጽ ተረክ በጥናቱ ቀርቧል። ይህ ተረክ የገዳሚን ህልውና የሚጠብቅ የልዕለ ተፈጥሮ እገዛ እንዳለ በማሳየት ገዳሚን የሚጻረርና የሚያፈርስ አካል ተጽዕኖ እንደሚደርስበት በማሳየት የገዳሚን ክብርና ሉዓላዊነት የማጠንከር ተግባር አለው።

በመሪማ ጥናት የቀረበው ተረክ ደግሞ ንዋየ ቅድሳቱን ሰርቆ ሊወስድ የመጣ ሌባ ሲያዝ የነበረውን ሂደት እንዲህ ይገልጻል። "የዕቃ ቤት ጠባቂው እንደ ወትሮው በሰዓቱ ተኝቷል። ዕቃ ቤቱ ግን በተመሳሳይ ቁልፍ ተከፍቶ ሌባው ንዋየ ቅድሳቱን እየሰበሰበ ነው። በዚህ ወቅት ቅድስት ድንግል ማርያም ለጠባቂው ተገልጣለት ተነሥ! ተነሥ!

ተነሥ! ስትል ከእንቅልፉ ነቅቶ ሌባውን ያስጥለዋል” (መሪማ፣ ፳፻፱፣ ገጽ ፶፩):: ይህ ተረክ የገዳሙን ሉዓላዊነት የሚጠብቀው ራሱ በገዳሙ የሚመሰገነው ቅዱስ መሆኑን ያሳያል:: በዚህ ተረክም ጠባቂው ብቻውን ገዳሙን እንደማይጠብቅ፤ በእሱ አማካኝነት ራሱ ፈጣሪ ቤቱን እንደሚጠብቅ የማሳየት ተግባር አለው:: ስለዚህ የገዳማቱን ልዕልና የሚያስከብረው ሰው ብቻ ሳይሆን ፈጣሪ እንደሆነ በተረኩ ተገልጿል::

**መ. ተአምርን ለማሳየት የሚተረኩ ተረኮች ፋይዳ**

ተዓምር የእምነቱን ተከታይ በእምነቱ ለማጽናት፣ የማያምነውን ደግሞ ከተዓምሩ ትምህርት እንዲያገኝ የማድረግ ኃይል አለው:: ተዓምር ሙት በማንሳት፣ የጎበጠ በማቅናት፣ ከአጋንት ምርኮ በማላቀቅ፣ ከለምጽ በማንጻት፣ ለዓይነ ሥውር ብርሃን በመስጠት፣መስማት የተሳነውን እንዲሰማ በማድረግ፣ ከሕግ ያፈነገጠውን በመቅጣት ይፈጸማል (Sulmasy, 2008):: በዚህ መልክ የሚገለጽ ተአምር አማኙ ፍጹም የሚመለከተውና የሚጠብቀው ፈጣሪ እንዳለ በመረዳት ለሃይማኖቱ እንዲገዛ የማድረግ ተግባር አለው:: በዚህ መሠረት በደብረ ሊባኖስ ገዳም ላይ በተጠናው ጥናት ውስጥ የቀረበ አንድ ተረክ እናገኛለን:: “አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ነገር ግን ጣዖትንም የሚያምን ሰው ሞቶ ደብረ ሊባኖስ ሊቀበር ሲመጣ ምድሪቱ አልቀበልም በማለት አስቸገረች:: በመጨረሻ በግድ ቆፍረው ቀብሩት፤ ቀባሪዎቹ ከቤታቸው ሲደርሱ አስክሬኑ ከጓሮ ሆኖ አገኙት (ዮሴፍ፣ ፳፻፯፣ ገጽ ፷፬)::ይህ ተረክ የሃይማኖቱን ሕግጋት ሳይፈጽሙ ለሚኖሩ ሰዎች ቅጣትም እንዳለ ይህም በዕለት ተዕለት ሕይወት ከተለመደው ውጪ (ተአምራዊ) በሆነ ክሥተት የሚገለጽ መሆኑን ያሳያል::

በዚሁ ጥናት የቀረበው ሌላው ተረክ “አንድ ገበሬ እርሻ ሲያርስ ሃይማኖታዊ ቁስ አግኝቶ ከጎተራው ቢከተው እህሉ በረከት አድሮበት በዛለት:: ከጓደኛው ጋር ሲጣላ ግን እኔ አይቸግረኝም ብሎ ተመጻደቀበት” (መሪማ፣ ፳፻፱፣ ገጽ ፷፩) :: ይህ ተረክ በመጀመሪያ የፈጣሪን የምሕረት ተአምር እህሉን በመባረኩ ሲበዛለት ያሳያል:: ይኸው ገበሬ በራሱ ያመጣው ምርት አለመሆኑን እያወቀ ከጓደኛው ጋር አነጻጽሮ ቢሰድበው እህሉ ባዶ ይሆንበታል:: በመሆኑም በተረኩ አማካይነት አማኞች የሚከወኑት ተግባር በፈጣሪ ፈቃድ እንደሚባረክላቸውና፤ ከፈጣሪያቸው ሕግጋት ሲያፈነግጡ የቍጣ ተአምር እንደሚደርስባቸው መልእክት መተላለፉ በጥናቱ ተገልጿል:: በመሆኑም በተረኮቹ አማካይነት በሚገለጹ ተአምራት አማኙ በእምነቱ እንዲጸና መልእክት ይተላለፋሉ::

### ፬.፪ በቃል ግጥም ላይ ያተኮሩ ጥናቶች አስተዋጽኦ

በዚህ ጥናት ለሃይማኖቱ አበርክቶ ካላቸው ጥናቶች በቀጣይነት የሚነሡት ቃል ግጥም ላይ ተመስርተው የተጠኑት ናቸው። በእነዚህም ጥናቶች ቃል ግጥም የሚደረድረው የሃይማኖቱ አባል ለተደረገለት ድኅነት ምስጋና፣ እንዲሆንለት ለሚፈልገው ነገር ተማጽኖ ወይም ልመና የሚያቀርብባቸው መሆናቸው በጥናቶቹ (ለምሳሌ ስመኘው፣ ፲፱፻፹፬ እና ተናኜ፣ ፲፱፻፺፱) ተገልጿል። በጥናቶቹም ቃል ግጥም በሚደረደርለት ቅዱስና በአማኙ መካከል ተዛምዶ እንዳለ የማሳየት፤ ሃይማኖቱም ለሌሎች ኢ- አማኞች እንዲታወቅ የማድረግ ተግባር እንዳለው መረዳት ይቻላል።

የስመኘው ጥናት የምለላ ግጥሞችን ከቅዱሳን ታሪክና ተአምራት እንዲሁም ከገድላትና ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እያነጻጸረ የቀረበ ነው። ቃል ግጥሞቹ የቅዱሳንን ስሞች የሚያነሱ፣ ብፁዕነታቸውን የሚያመለክቱ፣ አማላጅነታቸውን ለመጠየቅ ሲለምኑ፣ ሲሰብኩና ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸው በመሆናቸው ሃይማኖታዊ ዋጋቸው ከፍ ያለ መሆኑ በጥናቱ ቀርቧል። በጥናቱ የቀረቡት ቃል ግጥሞች የቅዱስ ላሊበላን ሥራዎች የሚገልጹ ከመሆናቸውም ባሻገር አማኙ ሕዝብ ቅዱሱን እንዲያከብር፣ እንዲዘምርለት፣ ወደ ቦታው ሄዶ የቃልኪዳን በረከት እንዲያገኝ የማድረግ ፋይዳ እንዳላቸው አጥኚው ገልጿል።

በዚሁ ጥናት በሌላ በኩል በጾመ ፍልሰታ የሚደረሱ የምለላ ግጥሞች ቅድስት ድንግል ማርያም የምትመሰገንበትና የምትለመንባቸው ግጥሞች መሆናቸው ተገልጾ የልመና ይዘት ያላቸው፣የማስተማር/ የመስበክ (የነፍስና የሥጋን ሕይወት) ይዘት ያላቸው፣ የውዳሴ (ለቅዱሳን፣ ለሰማዕታት፣ ለመላእክት) ይዘት ያላቸው፤ ልዩ ልዩ ተአምራትን የሚያሳዩ ግጥሞች (ቅድስት ድንግል ማርያም በስደቷ፣ በልጇ ስቅለት ጊዜ) ያሳለፈቻቸውን መከራዎች የሚያወሱ ግጥሞች በስመኘው (፲፱፻፹፬፣ ገጽ ፴፫) ቀርበዋል።

ማሳያ፡ ኦ! ማርያም እለምንሻለሁ ባሪያሽ
አንድ ጊዜ ስሚኝ ቀርበሽ
ተማልደሽ አማልጅኝ ከልጅሽ።

የቀረበው ቃል ግጥም በጾመ ፍልሰታ ለቅድስት ድንግል ማርያም ከተገጠሙ የልመና ቃል ግጥሞች አንዱ ሲሆን ተማጽኖን የማሳየት ፋይዳ አለው።

ሁለተኛው ጥናት በተናኘ (፲፱፻፹፱) የቀረበ ሲሆን፣ በዚህ ጥናት ርእስ ጎልቶ የሚታይ “መዋቲ” የሚል ቃል ይገኛል፡፡ ቃሉ ቅዳሴ ጸበል፣ የተጸለየበት ውኃ፣ ከመሬት የሚመነጭ ውኃ፣ ሲሆን መዋተኛ ማለት ደግሞ የታመመ ወይም ፈውስ የሚፈልግ መዋቱ ውስጥ በመግባት የሚታጠብ፣ የሚነከር፣ ወይም በመዋቱ የሚጠመቅ ሰው እንደ ሆነ በጥናቱ ቀርቧል፡፡ በጥናቱ እንደ ተገለጸው የልመና (ተማጽኖ) ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች አንድን የሆነ አካል ኃይል ለማኙ ወይም ተማጻኙ ያጣውን፣ የተቸገረውን፣ የፈለገውን እንዲያሟላለት የሚጠይቅበት ናቸው (ዝኒ ከማሁ)፡፡ በተጨማሪም አጥኚው ከሕመም ለመፈወስ የሚዜሙት ለመዋቱ/ ለጸበሉ ፈውስ እንዲሰጥ መዋተኛው በሰላም ከቤቱ እንዲመለስ ለመዋቱና የመዋቱ ቅዱስ ለሆነው ተማጽኖ የሚያቀርብባቸው እንደሆኑ አስፍሯል፡፡ እንዲሁም ቃል ግጥሞቹ መዋተኛው የፈወሰውን መዋት ትዝታ፣ ምስክርነት፣የምሥራች የመግለጽ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ቃልግጥሞች የአማኙንና የመዋቱን ቅዱስ ባለቤት ትስስር የሚፈጥሩ መሆናቸውን እንዲሁም የመዋትና የመዋተኛን ትስስር በቃል ግጥሞቹ አማካይነት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ለአብነት፦

ኧረ ተው! ማር መዋቱ
ኧረ ተው! ማር መዋቱ
ለታመመ ሁሉ ፈዋሽ መድኃኒቱ

የሚለው ግጥም ለአብነት ያህል (ዝኒ ከማሁ) ቀርበዋል፡፡ ከላይ እንደቀረበው የመዋቲዎች ቃል ግጥም መዋቲውን የመማጸን፣ የመዋቲው ቅዱስ ከሕመማቸው ሲፈውሳቸው የማወደስ ተግባራትን አሳይቷል፡፡ በመሆኑም አንባቢ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ቃል ግጥሞች ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውና በጥናቱ የተጠቀሰው ቅዱስ ስፍራ ተማጽኖና ተአምራት የሚፈጸምበት መሆኑን መረዳት ይችላል፡፡

### ፬.፫ የንዋየ ቅድሳትን አገልግሎትና ትእምርታዊነት

በዚህ ክፍል ቁሳዊ ባህልን ጉዳያቸው ያደረጉ ጥናቶች አበርክቶ እንደሚከተለው ተቃኝቷል፡፡ ጥናቶቹ በቃል ተረክ እንደቀረበው ሁሉ ንዋየ ቅድሳቱ ያላቸውን ፋይዳ ወይም ተግባር ማሳየት ላይ አተኩረው የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም በተቃኙት ጥናቶች በተመረጡት ሃይማኖታዊ ቁሶች አማካይነት ቁሶች ያላቸው ትእምርታዊ ፋይዳ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ቁሳዊ ባህሎች ተምሳሌታዊ ፍችን የያዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ በአገልግሎታቸው፣ በሚገለገልባቸው አካል መካከል ያለውን ዝምድና የማሳየት ተግባር አላቸው፡፡ በዚህ ክፍል የተካተቱት ጥናቶች አብዛኞቹ (ለምሳሌ የፍሬሕይወት፣ ፳፻)

ንዋየ ቅድሳትን ትኩረታቸው አድርገው ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ፋይዳቸውን ማሳየት ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡

በዚህ ክፍል ከተቃኙት ጥናቶች ውስጥ አንዱ የዐቢይ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት የምትጠቀምባቸውን የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅዱሳትንና አልባሳትን በዝርዝር ያሳየ ጥናት ነው፡፡ በዐቢይ ጥናት በቅጽረ ቤተ ክርስቲያ ውስጥ የሚገኙ፣ በመቅደስና በቅኔ ማኅሌት የሚገኙ ቁሶች፣ አልባሳት፣ በልዩ ልዩ ጊዜ የሚያገለግሉ ንዋያተ ቅድሳት (ቈፀማ፣ ባሕረ ጥምቀት፣ ዘምባባ፣ ደመራ እና ድባብ) አጫጭር መግለጫ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የመስዋዕት፣ የቅባት፣ የሽቱ ዓይነቶች ተብራርተዋል፡፡ እንዲሁም ጥናቱ የሃይማኖቱ መሪዎች የሚይዟቸውን ቁሶች ከነትርጓሜያቸው የማሳወቅ ፋይዳ አለው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በአጠቃላይ በሃይማኖት ተቋሙ አግልግሎት ላይ የሚውሉ ልዩ ልዩ የተቀደሱ ቁሶችን በማስተዋወቅ ረገድ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

የንዋየ ቅድሳትን ሃማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት ላይ ትኩረት ባደረገው የፍሬሕይወት ጥናት የቤተ ክርስቲያን ምንነትና ክፍሎቿ፣ የቤተ ክርስቲያን አሠራር፣ በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ የሚሠሩ ቤቶች፣ አልባሳት፣ መገልገያ ቁሶች በሙሉ ንዋያተ ቅድሳት እንደሚባሉ በመግለጽ ለአንባቢ አጠቃላይ መረጃ ይሰጣል፡፡ ይህ ደግሞ በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ ያለ አንባቢ ቤተ ክርስቲያንን የተመለከቱ መረጃዎችን እንዲገኝ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ጥናት የሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሠራር ሰቀላ፣ ክብ ቤት ንጉሥ እና ፍልፍል እንደሆኑ ተገልጾ የያንዳንዱን ትዕምርት ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ጥናት በመቅደስ የሚያገለግሉ ንዋያተ ቅድሳት፣ በመቅደስና በማኅሌት የሚያገለግሉ ንዋያተ ቅድሳት፣ ለማኅሌት የሚያገለግሉ፣ ከማኅሌት ውጭ የሚያገለግሉ በማለት አጥኚዋ ተምሳሌታቸውን አቅርባለች፡፡ በመሆኑም እነዚህን ንዋየ ቅዱሳት በሚመለከት አንባቢ መረጃ እንዲያገኝ ጥናቱ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በዳባት ገብርኤል ቤተ-መዘክር ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎችን መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር በማቅረብ የተጠናው የአንተነህ ጥናት በቤተ መዘክሩ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎችን ትንታኔ አቅርቧል፡፡ በዚህ ቤተ-መዘክር ውስጥ የምናገኛቸው አብዛኛዎቹ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት ከዓለማዊ ፍልስፍናና ከልብ ወለድ ታሪክ የተለዩ ስለ ቅድስናና ንጽሕና፣ ስለ ቅዱሳን፣ ስለ ሃይማኖት በሰፊው የሚያትቱ፣ ጸሓፊዎቻቸውም በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተመሩ በመሆናቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ይባላሉ (አንተነህ፣ ፳፻፩፣ ገጽ ፴፫) በማለት አስፍሯል፡፡ አጥኚው የንዋያተ ቅድሳቱን (ብራና መጽሐፍ፣

አልባሳት፣ ከበሮ፣ ጽናጽል፣ በገና፣ መሰንቆ፣ መስቀሎች) አገልግሎትና ተምሳሌት አሳይቷል።

በዚህ ክፍል የተቃኘው ሌላኛው ጥናት የተስፋዬ ጥናት ነው። በቁሳዊ ባህል የጥናቱ ክፍል ገዳማውያን የሚለብሷቸውን ቀሚስ፣ ቆብ፣ አስኬማ፣ቅናተ ዮሐንስና ሥጋ ማርያም፣ የሚይዛቸውን መቁጠሪያ፣ መስቀል፣ በትረ መስቀል በሚል ከዘረዘራቸው በኋላ ትርጓሜያቸውን አቅርቧል። እንዲሁም የአመጋገብ ሥርዓታቸውን፣ የሥራ ክፍፍላቸውን ገልጿል። ትንተናውም በሃይማኖቱ ከሚሰጠው ሕግና ትእምርት አንጻር እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል። በዚሁ ጥናት መነኮሳትና መነኮሳይያት የሚለብሷቸው ቀሚሶች የተለያዩ መሆናቸው ተገልጿል። በጥናቱ እንደተገለጸው ቢጫ መልበሳቸው ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ ሕይወትን መሻታቸውን ያሳያል። ወይባ መልበሳቸው በዓለም ከሚኖረው ሕዝብ በታች ነን፤ ስለ ክርስቶስ ፍቅራችንን ጥለን እንኖራለን ሲሉ የሚለብሱት ነው። ጥቁር መልበሳቸው በዓለሙ ኃጢያት አዝኛለሁ፤ በሐዘን እኖራለሁ ሲሉ ይለብሱታል (ተስፋዬ፣ ፳፻፫፣ ገጽ ፶፰)። በቀረበው መረጃ መሠረት የአልባሳት ቅርጽና ቀለም ሃይማኖታዊ ተምሳሌት አለው። በመሆኑም አንባቢ ከዚህ ጥናት በሚገኝ መረጃ በእውኑ ዓለም የሚያያቸውን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን አልባሳትና ቀለማቸውን ትርጓሜ እንዲረዳ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በተጨማሪም ቆብ፣ የአንገት ማዕተብ፣ አስኬማ፣ መቁጠሪያ እና መስቀል የተባሉት ንዋየ ቅድሳት ዓይነታቸውና ለልዩነታቸው ምክንያት የሆነው ትርጓሜ/ ተምሳሌት በዚሁ ጥናት በዝርዝር ቀርቧል።

በሌላ በኩል በምህረት ጥናት ቁሳዊ ባህልን የተመለከተ መረጃ በቀረበበት ክፍል የገዳማውያኑን አመጋገብ፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች ከሃይማኖታዊው ሥርዓትና ትርጓሜ አንጻር ተንትኗል። በዚህ ጥናት (ምሕረት፣ ፳፻፫፣ ገጽ ፶፱) በዘመነ ኦሪት ጊዜ መሥዋዕት ይቀርብባቸው የነበሩ ቁሶች ቀርበዋል። የመጀመሪያው የድንጋይ መንበር ሲሆን ለስድስት መቶ ዓመት ያህል መሥዋዕት እንደ ቀረበበት በመግለጽ ከእሥራኤል ቀጥሎ አምልኮተ እግዚአብሔር የተጀመረበት ጥንታዊ ገዳም መሆኑን የሚያመለክት እንደሆነ አጥኚው ገልጿል (ዝኒ ከማሁ)። የመሥዋዕቱ ድንጋይ ራሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት መሆኑን በጥናቱ ተገልጿል። በመሪማ በቀረበው ጥናት ደግሞ በቁሳዊ ባህል የብራና መጻሕፍት፣ መሶበወርቅ፣ የቅድስና ዋሻ፣ የሰጎን እንቁላል ደወል እና መስቀል ያላቸው ሃይማኖታዊ ትእምርት ቀርቧል። ስለዚህ እያንዳንዱ ንዋየ ቅድሳት የራሱ ተምሳሌታዊ ፍች ያለው መሆኑን የማሳየት ፋይዳ አለው።

በአጠቃላይ በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥናቶች የንዋየ ቅድሳት ዓይነቶችና ትእምርታዊ ትርጉማቸውን የተነተኑ ናቸው:: በመሆኑም የማንበብ አጋጣሚውን ላገኘ አንባቢ አይነቶቹን እያንዳንዳቸውም ያላቸውን ሃይማኖታዊ ተምሳሌት በሚመለከት መረጃ ይሰጣሉ::

## ፭. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የይሁንታ ሐሳቦች

ይህ ጥናት በሃይማኖታዊ ፎክሎር ላይ የተካሄዱ ጥናቶችን የመረጃ ምንጭ አድርጎ የተካሄደ ነው:: በጥናቱም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚገኘው የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የሃይማኖት ፎክሎርን ጉዳያቸው ያደረጉ የመመረቂያ ጥናቶች ለጥናታቸው መዳረሻ ለመረጡት የሃይማኖት ተቋም ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ተፈትሿል:: የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ለመጀመሪያና ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናቶች በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል::

ጥናቶቹም የፎክሎር ዘርፎችን አንዱ ወይም ሁለቱን አጣምረው ያጠኑ ሲሆኑ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት ሥነ ቃል እና ቁሳዊ ባህልን ነጣጥለው እና አጣምረው ያጠኑት ናቸው:: ለጥናቱ ከተመረጡት ፲፪ ጥናቶች ሁለቱ ቃል ግጥምን፣ አራቱ ተረክን፣ ሦስቱ ቁሳዊ ባህልን ነጥለው ያጠኑ ሲሆኑ የቀሩት ሦስቱ ደግሞ ቁሳዊ ባህልን እና ሥነ ቃልን አጠምረው ያጠኑ ናቸው::

ጥናቶቹ በሁለት ንኡስ ምዕራፎች ተከፋፍለው ትንተና ተደርጎባቸዋል:: የተመረጡት የሃይማኖት ፎክሎር ጥናቶች ተለይተውና ተዘርዝረው የቀረቡበት የመጀመሪያው ነው:: ሁለተኛው የጥናቶቹን ትኩረትና አበርክቶአቸውን አጣምሮ የያዘው ሲሆን ጥናቶቹ ሥነ ቃል (ቃል ተረክና ቃል ግጥም)ን ያጠኑ፣ ቁሳዊ ባህልን ያጠኑ እና ቁሳዊ ባህል እና ቃል ተረክን አጣምረው ያጠኑ በሚል ተከፋፍለው ለሃይማኖት ተቋሙ ያላቸው አበርክቶ መረጃዎችን በማቅረብ የተተነተነበት ነው:: በዚህ መሠረት በጥናቱ ትንተና የታዩ ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው::

በጥናቶቹ የቀረቡት ተረኮች የገዳሙን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት፣ ቅድስናና የቦታውን ክብር ከፍ የሚያደርጉ፣ የሃይማኖቱንና የአማኙን ትስስር የሚያጠናክሩ ናቸው:: በዚህም የአማኙን እምነት የማጠናከርና የመትክል ተግባር የሚያሳዩ ናቸው:: ሁሉም ጥናቶች በአብዛኛው ማስረጃቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክና ከሃይማኖቱ አማኞች ዘንድ ያደርጋሉ:: ይህም የሃይማኖት ተቋሙን የማስተዋወቅ ረገድ ሚና እንዲኖራቸው አድርጓል:: በሌላ በኩል ጥናቶቹ በርእሳቸው የሚያጠኑትን ደብር ወይም ገዳም ስም

ይጠቅሳሉ። ይህ ደግሞ እያንዳንዱ ጥናት ቢያንስ አንድ ቅዱስ ሃይማኖታዊ ቦታን በስም የማስተዋወቅ ሚና እንዲኖረው ምክንያት ሆኗል።

ቁሳዊ ባህልን ጉዳያቸው አድርገው የተካሄዱት ጥናቶች በዋናነት ንዋየ ቅድሳት ላይ ትኩረት ያደረጉ ሲሆኑ ንዋየ ቅድሳቱን በስም ከመጥቀስ ባለፈ ተምሳሌትነታቸውን በዝርዝር ያቀረቡ በመሆናቸው ሃይማኖታዊ ዕውቀትን በማሻገር ረገድ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ትንተናው አመላክቷል። በመሆኑም ከንባብ ከሚገኝ ዕውቀት ባለፈ አንባቢ ቦታዎቹን ለመጎብኘት ፍላጎት እንዲያድርበት ተነሣሽነትን ይፈጥራሉ። አንባቢ ከጥናቶቹ በሚያገኘው መረጃ ቦታዎቹን የመጎብኘት አጋጣሚ ቢፈጠር ደግሞ እነዚህን ገዳማት እና አድባራት የቱሪዝም መዳረሻ በማድረግ ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የጎላ ነው። በዚህ ጥናት የተቃኙት ጥናቶች ከቀረቡለት የትምህርት መስክ በተጨማሪ ሃይማኖትን ጉዳያቸው ያደረጉ በመሆናቸው የሃይማኖት ተቋሙን በማስተዋወቅ ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አላቸው። በመሆኑም፡

- ❖ በየጊዜው የሚጠኑት ጥናቶች በሃይማኖቱም ሆነ በፎክሎር ዘርፍ ባሉ አጥኚዎች እየተቃኙ ያላቸው አበርክቶ ቢፈተሽ መልካም ነው።
- ❖ በአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በፎክሎር ዘርፍ የሚቀርቡት እነዚህ ጥናቶች አበርክቶአቸውን ከግምት በማስገባት የሃይማኖት ተቋሙና ትምህርት ክፍሉ መረጃ የሚለዋወጡበት አጋጣሚ ምርምርን ጉዳያቸው ባደረጉ የሁለቱም ተቋማት ክፍሎች በኩል ቢፈጠር፣
- ❖ አንድን የሃይማኖት ተቋም የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ የሃይማኖት ተቋሙ ብቻ ሳይሆን ተዛማጅነት ባላቸው መስኮች የሚሠሩ ጥናቶችም የራሳቸው አበርክቶ ያላቸው ለመሆናቸው በዚህ ጥናት የቀረበው መረጃ አንዱ ማሳያ ነው። በመሆኑም የሃይማኖት ተቋሙ ውስጥ ያሉ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ጥናትና ምርምርን ጉዳያቸው ያደረጉ የሚዲያና የኅትመት ክፍሎች ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የመረጃ ምንጫቸው አድርገው በሚሠሩ መስኮች የሚጠኑ የጥናት ሥራዎች ለሃይማኖታዊ ተቋሙ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የሚቃኝበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ሰጥተው ቢሠሩ መልካም ነው።

## ዋቢ ጽሑፎች


መሪማ መሐመድ:: (፳፻፱)::*የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረትና በገዳሟ ዘሪያ የሚነገሩ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት* [ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ] :: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት::

ሚሊዮን በለጠ:: (፳፻፰):: *ንዋየ ቅድሳት፡ አዘገጃጀት አጠቃቀምና ምሥጢር::* www. ethiopian orthodox.org

ምሕረት ተስፋዬ:: (፳፻፫):: ``*ከጣና ቂርቆስ አንድነት ገዳም አመሠራረት ተረኮችና ቁሳዊ ባህል ጥናት*`` [ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ] :: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሐፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት::

ስመኘው አራጌ:: (፲፱፻፹፬):: ``*በጸመ ፍልሰታና በንግስ ላሊበላ የሚደረሱ የምለላ ግጥሞች*`` [*ያልታተመ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ*] :: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሐፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል::

ተስፋዬ ተገኘ:: (፳፻፫):: ``*የደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ አንድነት ገዳም አመሠራረትና ቁሳዊ ባህል ጥናት*`` [ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሐፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት::

ተናኘ አበበ:: (፲፱፻፺፱):: ``*በደቡብ ጎንደር ዞን በሚገኙ መዋቶች በተጠቃሚዎች የሚዜሙ ቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና*`` [ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣::

ቴዎድሮስ ይበልጣል:: (፳፻፰)::የደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም አመሠራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና [*ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ*]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሐፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት::

ቴዎድሮስ ገብሬ:: (፳፻፩):: *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፡-ሥነ ጽሁፍ እና ሚቶሎጂ፣ ፍልስፍና ፣ ሥነ ልቡና::* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ዐቢይ ፍትሐ ዐወቅ:: (፲፱፻፷፫):: *``የሕንፃ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳትና የአልባሳት ስሞች``* [ያልታተመ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት::

አንተነህ ደሴ:: (፳፻፩):: *``በዳባት ገብርኤል ቤተ-መዘክር ውስጥ የሚገኙ ቁሳዊ ባህሎች መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫ ጋር``* [ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት::

ወንድወሰን ሞላ:: (፳፻፯):: *``በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት``* [ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት::

ዮሴፍ ቦኪ:: (፳፻፯):: ``የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ተረኮች ጥናት`` አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሐፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ::

ፈቃደ አዘዘ:: (፲፱፻፺፩):: *የሥነ ቃል መምሪያ::* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

ፍሬሕይወት ባዩ:: (፳፻):: *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ* [ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ::

ፍጹም ኩራባቸው:: (፳፻፮):: የዝዋይ ደሴት ገዳማትና አድባራት ተረኮች ጥናት [ያልታተመ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሐፍ]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት::

Bascom, R. W. (1954). Four functions of folklore. The Journal of American Folklore, 67(266): 333-34. https://www. jstor.Org/stable/53641.

Dorson, M. R. (Ed). (1972). Folklore and folklife: An introduction. The University of Chicago Press.

Ghelawdewos A. (2017). The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church: History, doctrine, and challenges. Institute of Development and Education for Africa (IDEA). https://www.africanidea.org/Ethiopian_Orthodox_Tewahedo.pdf

Gustavsson, A. (2012). Cultural studies on folk religion in Scandinavia. Novus Press.

Kamppinen, M. (2014). The role of theory in folkloristics and comparative religion. Approaching Religion,4(1): 3-12.

Phunoug, A. L. (2021). How Did Folklore Reflect Religion.https://doi.org.10.31219/osf.io/pa6t3

Sariors, Cara Leigh. (2007). The Fanction of mythology and religion in ancient Greek society [Master'sthesis]. School of Graduate Studies, East Tennessee State University.

Sulmasy, D. (2008). What Is a Miracle? Southern Medical Journal, 100, 1223–1228. https://doi.org/10.1097/SMJ.0b013e31815a9784

Szonyi ,V. (2018). The social embeddedness of the dance culture in a Moldavian village. Open Journal for Anthropological Studies, 2018, 2(2), 37-52.

Zerihun D. (2005). Introduction to Sociocultural Anthropology. https://doi.org/10.13140/2.1.3435.6484